# አለቃ ዶ/ር አየለ ዓለሙ

## /፲፰፻፹፯ – ፲፱፻፹፱/

በመሠረት ከበደ



አራት ዓይና ዶክተር

የሃያኛ ዓመት የዕረፍታቸውን መታሰቢያ አስመልክቶ ጥር ፲፮ ቀን ፲፱፻፸፪ ዓ.ም በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት የታተመው መጽሔተ ሊቃውንት «የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ሊቅነታቸውን በመረዳት በ፲፱፻፷ ዓ.ም በሰኔ ወር የዶክተርነት ማዕረግ ሰጥቷቸዋል። .በዚህም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት የመጀመሪያውና ብቸኛው ናቸው። የሊቃውንት ኮከብ የተባሉትም ስለዚህ ነው» በማለት ስለእኚህ ታላቅ የቤተ ክርስቲያን ሊቅ ገልጿል።

አለቃ ዶክተር አየለ ዓለሙ የክብር ዶክትሬት ከተቀበሉ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት የመጀመሪያው ናቸው። ከዚህ መዓርግ በተጨማሪ አራት ዓይና የሚል የቤተ ክርስቲያን መዓርግ አላቸው። ይህ መዓርግ የሚሰጠው በቤተ ክርስቲያን ትምህርት የጠለቀ ዕውቀት ላላቸው አራቱን ጉባኤያት ለሚያስተምሩ ሊቃውንት ነው። አራቱ ጉባኤያት የሚባሉት መጻሕፍተ ብሉያት፣ መጻሕፍተ ሐዲሳት፣ መጻሕፍተ ሊቃውንት እና መጻሕፍተ መነኰሳት ናቸው። መጻሕፍተ ብሉያት አጠቃላይ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን የሚያጠቃልል ሲሆን መጻሕፍተ ሐዲሳት አራቱን ወንጌላውያንና የጳውሎስ መልእክታትና ሌሎቹ ይጠቃለላሉ። መጻሕፍተ ሊቃውንት ውስጥ የሚካተቱት ፍትሐ ነገሥት፣ ቄርሎስ፣ ዮሐንስ አፈወርቅ፣ ሃይማኖተ አበው፣ መጻሕፍተ ቅዳሴያትና የመሳሰሉት

ናቸው:: መጻሕፍተ መነኰሳት የመነኰሳትን ተጋድሎና ክብር የሚ
ናገሩና ማር ይስሐቅ፣ አረጋዊ መን ፈሳዊና ፊልክስዩስን ያካተተ መጽሐፍ
ነው:: አለቃ ዶ/ር አየለ ዓለ ሙም የነዚህ ሁሉ ዐዋቂ ናቸው::

በይነ ምንት ዘተኀብአ ኪዳነ ማርያም ዕንቈ ባሕርይ ያበርህኑ፣
ለምድር ውስቴታ ሥነ ጸዳሉ አእምሮ፣
ወአርድእት ኃለፍት ትርጓሜ ይክሉኑ ነጽሮ፣
ገጸ መጻሕፍት አድባር ዘሙሴ መጽሔተ ገጹ ተምህሮ፣
እስመ ለጉባኤነ ተሠወሮ፣
ወእፎመ ሞት ኀምዘ ተፅዕሮ፣
ለመዓር ልሳኑ አምረሮ::

አለቃ ዶ/ር አየለ ዓለሙ ባረፉ ጊዜ ከቀረቡት ቅኔዎች መካከል
አንዱ ዶ/ር አየለ ዓለሙ የተወለዱት ጐንደር ጭልጋ አውራጃ በዳዋ
ወረዳ ይተና ማርያም የተባለች ቦታ ነው:: አባታቸው አቶ ዓለሙ ኪ
ዳነ ማርያም እናታቸው ደግሞ ወ/ሮ ማን አህሎሽ ወ/ጊዮርጊስ ይባ
ላሉ:: ዶክተር አየለ በ፲፱፻፳፯ ዓ.ም ተወለዱ::

ሕፃን አየለ አባታቸውን ያጡት ገና በልጅነታቸው ነበር:: እናታ
ቸው ወ/ሮ ማን አህሎሽ ባለቤታቸው በሞት ከተለዩዋቸው በኋላ ልጃ
ቸውን አየለ ዓለሙን ይዘው ወደ ትውልድ መንደራቸው ገንደዋ
ገብርኤል ሔዱ:: ጐንደር አውራጃ ከመምጣታቸው በፊት አየለ ዓለሙ
እዛው የትውልድ ቦታቸው አቦ ገዳም መሪጌታ ሳህሉ ጋር ትምህርት
ጀምረው ዳዊት ላይ ደርሰው ነበር:: አለቃ አንድ አጐት ነበሯቸው::
የዜማ መምህር የድጓ መምህር የሆኑት እኚሁ አጐታቸው አለቃ አበራ
ይባላሉ:: አለቃ ወ/ሮ ማን አህሎሽን ያስፈቅዱና ሕፃኑን አየለን ጐን
ደር አዘዞ ተክለሃይማኖት ወሰዷቸው:: አእምሯቸው በስሎ ራሳቸውንም
እስኪችሉ በማለት አለቃ አበራ ከእርሳቸው ጋር እንዲኖሩ ያደርጋሉ::
ወደ ሌላ ትምህርት ቤት የሚሔዱበት ቀን እስኪደርስ በዜማ ትም
ህርት እየበሰሉ ሔዱ:: እንደውም አንዳንዴ አለቃ ተማሪዎቻቸው
ቀለም ሲጠሩቸው ለማትጋት አየለን እንዲጠይቁ ለተማሪዎቹ ይነግራ
ሉ:: የአዘዞ ተክለሃይማኖት ደብር ታላላቅ ሊቃውንትም አየለ ዓለሙ





ሲቃኙ መስማት ይወዱ ነበር:: ዐቢይ ጾም በመጣና ጾመ ድጓ በተቆመ
ቁጥር «አየለ ይቃኘው» ይሉ ነበር:: በዚህ ሁኔታ ወደ ትምህርት ዓለም
የገቡት አለቃ ዶክተር አየለ ዓለሙ በአንድ ወቅት በአንድ መምህራ
ቸው «ፍላቴ» በሚል ቅፅል መጠሪያ ይጠሩ ነበር:: መምህሩ በተማሪ
ያቸው የቀለም መያዝ ስጦታ በመደነቅ ነበር ይህን መጠሪያ የሰጧቸው::

## ጠባይዕ

አለቃ ዶክተር አየለ ዓለሙ በብዙዎች ዘንድ የሚታወቁት በትኅት
ናቸው፣ ባላቸው ከፍተኛ ቀለም የመያዝ ስጦታ፣ በርኅሩኅነታቸውና ደከ
መኝ ሰለቸኝ የማያውቁ በመሆናቸው ነው:: ስለ ትኅትናቸው የበጌ
ምድርና የሰሜን ክፍለ ሀገር ሊቀ ጳጳስ የነበሩት ብፁዕ አቡነ እን
ድርያስ እንዲህ ብለው ነበር:: «ዶ/ር አለቃ አየለ ብዙ ደቀመዛሙ
ርትን ተክተውልን አልፈዋል፤ ከትኅትናቸውና ከትዕግሥታቸው ግን
አንድም አልተኩልንም»:: ቀለም ቶሎ የመያዝ ብቻ ሳይሆን ያለመዘን
ጋት ችሎታም ነበራቸው:: ይኸው ስጦታቸው ነበር «ፍላቴ» የሚለውን
የአድናቆት ስም ያሰጣቸው:: ተከታዮቻቸውና ተማሪዎቻቸው አራቱን
ጉባኤያት አለቃ በሚያስተምሩ ጊዜ ቀለም በመዘንጋት አለመቸገራ
ቸውን እያዩ እንደሳቸው መሆንን እየተመኙ ችሎታቸውን ያደንቁ ነበር::

አለቃን የሚያውቁ ስለ ጠባያቸው ሲናገሩ የርኅሩኅነታቸውን ነገር
ያስታውሳሉ:: ለጋስ እንደሆኑ ይነገራል:: አንድ ጊዜ ገንዘብ ያዥ
ያቸውን ስንት ብር እንዳለ ይጠይቃሉ:: እሱም አንዲት አምስት ብር
እንደቀረች ይነግሯቸዋል:: ይወስዱና ወደ ውጭ ወጥተው «ማን ነው
ገንዘብ ያልደረሰው?» ብለው ይጠይቃሉ:: በአጋጣሚ የደረሰ ችግረኛ
«እኔ አለሁ» ብሎ ብሯን ተቀብሎ ሄደ::

አለቃ አየለ ዓለሙ ታላቅ መምህር ስለነበሩ በንጉሠ ነገሥቱ ዐፄ
ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ቀለብ ይሰጣቸው ነበር:: ይህን ቀለብ ይወስ
ዱና ለችግረኞች ያከፋፍላሉ:: የሚሰጣቸውንም ገንዘብ በየጐ ዳናው
ላሉ ችግረኞች አከፋፍለው ወደ ቤታቸው ይገባሉ:: ይህ ዝናቸው በጐ
ንደር አካባቢ ባሉ ሥፍራዎች ሁሉ ታወቀ:: ጎንደር አውራጃ በጉባኤ
ማስተማር ሲጀምሩ በርካታ ተማሪዎች ወደሳቸው መጡ:: ቀለብ

ተካፋዩ ሲበረክት የሚያገኘውም ይበዛ ጀመር:: ስለዚህ አንድ ዘዴ
አመጡ አለቃ በገንዘብ ያኙው በኩል ቀለባቸው ለችግረኞቹ እንዲ
ከፋፈል ተደረገ::

ይህን ተግባራቸውን መንግሥት ስላወቀ የዕለት ምግብ ከቤተ መን
ግሥት ተፈቀደላቸው:: በዚህ ጊዜ በየደጀሰላሙ ያሉ ደጅ ጠኚዎች
ነገር አሳሰባቸው:: ሊጠይቋቸው ሲመጡም ለመለመን ያፈሩ ግን በረ
ሀብ አለንጋ የሚገረፉ መሆናቸውን ስለሚያውቁ ከዕለት ድርጓቸው
ያካፍሏቸዋል:: አሁንም በምግብ እየተጐዱ መሆኑ ሲታወቅ የእንግዳ
መቀበያ ተፈቀደላቸው::

እንደዚህ አድርገው ድንገት ችግረኛ የመጣባቸው ከሆነና የሚሰ
ጡት ከሌለ ከደቀመዛሙርታቸው ይበደሩና ይሰጣሉ:: አለበለዚያ ከመ
ንግሥት ባለ ሥልጣናት የችግረኞች መርጃ እየጠየቁ ያመጡና ተማሪ
ዎቻቸውንና ድሆችን ይረዱ ነበር::

አለቃ ዶክተር አየለ ዓለሙ ወገኖቻቸውን መርዳት በጣም ይወ
ዳሉ:: ባለ ጉዳይ ሲጉላላ ደስ አይላቸውም:: እጅ ለመንሣት ባለሥል
ጣናት ጋር በሚሔዱ ጊዜ ባዶ እጃቸውን አይገቡም:: የባለ ጉዳዮችን
ደብዳቤ ይዘው ይሔዱና ሲወጡ ባለሥልጣኑ ፊት ደብዳቤዎቹን አስ
ቀምጠው ይወጣሉ:: ይህ ድርጊታቸው አንዳንድ ባለሥልጣናትን ቢያስ
ከፋም ብዙዎቹ ይወዱላቸዋል:: ባለ ሥልጣን ጋር የሚያደርሳቸው ያጡ፣
ፍትሕ ርትዕ የሚሹ ወገኖችን ጉዳይ ይዘው እንደሚመጡ ያውቃሉና::
እሳቸውም ራሳቸውም ቢሆኑ ባለሥልጣናቱ እንዳይቀየሙ የድሆች ዕንባ
መፍሰስና የፍትሕ ርትዕ መታጣት ሀገርን እንደሚጐዳ በመግለፅ ነገ
ሩን ያስረዷቸዋል::

አለቃ አየለ ለብዙዎች በድካማቸው ጊዜ ኃይል ናቸው:: ደከመኝ
ሰለቸኝ ብለው የሚያስታጉሉት ነገር የለም:: በጸሎትም በማስተማርም
የተጉ ናቸው:: ይህን ጠባያቸውን የሚያውቁ በ፩ኛ ጢሞ ፬፥፲፭-፲፪
የሚገኘውን «ምክር አስተምር በቃልና በኑሮ በፍቅርም በእምነትም በን
ጽሕናም ለሚያምኑ ሁሉ ምሳሌ ሁን እንጅ ማንም ታናሽነትህን አይና
ቀው እስክመጣ ድረስ መጽሐፍ በማንበብና በመምከር በጸሎትም ተጠ





ብቀህ ኑር:: ይህንም አዘውትር:: እንዲህ ያደረግህ እንደሆነ ራስህንም
የሚሰሙህንም ታድናለህ» የሚለውን የቅዱስ ጳውሎስን ምክር በተግባር
የገለፁ ይላቸዋል::

እኚህ ታላቅ ሊቅ ከማለዳው አሥራ አንድ ሰዓት አንሥተው እስከ
ሰባት ሰዓት ድረስ አራቱን ጉባኤያት በተራቸው ሲተረጉሙና ሲ
ያስተምሩ ይውላሉ:: እንዲህም ሆኖ የተማሪዎቻቸው ቁጥር በርካታ
ስለሆነ እያንዳንዱ ተማሪ አይደርሰውም:: ከሰዓት በኋላ ምግባቸውን
በአስቸኳይ ቀምሰው ወደ ጉባኤያቸው ተመልሰው ለነገው ጉባኤ ይዘጋ
ጃሉ:: የተዛባውን ምሥጢር ለማቅናት የጐደለውን ለመሙላት መጻሕ
ፍቱን ያስነብባሉ:: አንዳንድ ጊዜ አላልቅ ይልና ሲጨልም በመብራት
ያስነብቡና ወደ ማታ ጸሎታቸው ይገባሉ:: ጥቂት ያርፉና ደግሞ
የመንፈቀ ሌሊት ጸሎታቸውን ዝግ ባለ ሁኔታ ያደርሳሉ::

## መማር /ማስተማር

ወጣቱ ተማሪ አየለ የዜማው ትምህርት ቢስማማቸውም ቅኔ መማር
ስለፈለጉ ከዜማ መምህራቸው ከአለቃ አበራ ፈቃ ጠይቀው የአደራ
ደብዳቤ ጭምር ተሰጥቷቸው መምህር አባተ ዘንድ ጐንቢያ ወረዳ አረ
ቢያ መድኃኔዓለም ተላኩ::

አየለ ቅኔ መቁጠር ጀመሩ:: ትምህርቱ በጣም ከበደባቸው:: ቢሆ
ንም ተስፋ ባለመቁረጥ ትምህርታቸውን መከታተል ቀጠሉ:: በመጨ
ረሻ ወደ ቀድሞ ትምህርት ቤታቸው ለመመለስ ይወስኑና ጓዛቸውን
ጠቅለለው መንገድ ይጀምራሉ:: ጓደኞቻቸውም እንዲቀሩ ቢለምኗቸው
በጄ ስላላሏቸው ጉዳዩን ለመምህራቸው ይናገራሉ:: መምህር አባተም
ለተማሪዎቹ መልእክት ላኩ:: በአካባቢው ድርማ የሚባል ወንዝ አለ::
«ሂዱና ድርማን ሳይሻገር ያገኛችሁት እንደሆነ እንደ ምንም ብላችሁ
ይዛችሁት ኑ:: ወንዙን ተሻግሮ ካገኛችሁት ግን ተውት» ይላቸዋል::
ደቀ መዛሙርቱም በፍጥነት ቢሔዱ አለቃ ወንዙን ሳይሻገሩ ከወንዙ
ዳር ከነበሩ ከብት ጠባቂዎች መንገድ ሲጠይቁ አገኟቸው::

በዚህ ሁኔታ ወደ ቅኔ ትምህርታቸው የተመለሱት ደቀ መዝሙሩ
አየለ በኋላ ያስቸገራቸውን ቅኔ ተካኑት:: ቅኔን እስከነ አገባቡ

አውቀው አሉ የተባለ ቅኔ ዘራፊ ሆኑ:: ያውም የመምህራቸው ምክትል:: በዚሁ አገልግሎት ረዘም ላለ ጊዜ ከቆዩ በኋላ ወደ አዘዞ መመለስ ግድ ሆነባቸው:: አጐታቸው አለቃ አበራ የዜማውን ትምህርት እንዲያጠናቅቁና ወደ ቤተልሔምም ሄደው ድጓውን እንዲያስመርቁ ልከውባቸው ወደ ቤተልሔም አቀኑ:: ቤተልሔም እየተማሩ ሳለ አለቃ ኀሩይ ፈንታ የተባለ የመጽሐፍ መምህር የመጻሕፍትን ትርጓሜ እንዲማሩ ጠሯቸው::

ወዲያውም የቄርሎስን ትርጓሜ አጠኑ:: ከዚያም የመጻሕፍት ትርጓሜን የበለጠ ለመማር ጎጃም ደንበጫ ቅዱስ ሚካኤል ከአለቃ ተስፋ ዘንድ የሃይማኖተ አበውን ትርጓሜ መማር ጀመሩ:: አለቃ ተስፋ ወደ ሞጣ ጊዮርጊስ ተዛወሩ:: የደንበጫ ካህናት አለቃ አየለ በአለቃ ተስፋ ቦታ እንዲተኩ ፈልገው ነበር:: እርሳቸው ግን ሞጣ ሄደው የመጻሕፍተ ሊቃውንትን ትርጓሜ አውቀው መምህርነታቸውን አስመርቀው ጐንደር ተመለሱ:: እኚህ መምህራቸው አለቃ ተስፋ ነበሩ «ፍላቴ» ብለው የሚጠሯቸው::

ከጐጃም ተመልሰው ጐንደር ግምጃ ቤት ማርያም ከታላቁ ሊቅ መምህር ተክለ ማርያም የሐዲሳትን ትርጓሜ ሲያሔዱ ቆዩ:: ቀጠሉና ሐዲሳቱን ለማጠናቀቅ ሰሜን አውራጃ ደረስጌ ማርያም ከመምህር ገብረ ማርያም ዘንድ ሔዱ::

ከሰሜን ደግሞ ወደ ጐንደር ተመለሱና ከጌታው አለቃ ዘዮሐንስ ዘንድ የፍትሐ ነገሥትን ትርጓሜ መማር ጀመሩ:: የሊቃውንቱን ትርጓሜ ደግሞ በጐን ያስተምሩ ነበር:: በዚህ ጊዜ መምህሮቻቸው አለቃ ኀሩይና አለቃ ተስፋ ከጌታው አለቃ ዘዮሐንስ ጋር መጡ:: ጉባኤውም ይሰፋ ጀመር:: አለቃ አየለ ለመምህሮቻቸው የማስተማሩን ሥራ ለመልቀቅና የፍትሐ ነገሥቱን ትርጓሜ ለማጠናቀቅ ወሰኑ:: እነ አለቃ ተስፋ ግን ከእንግዲህ ማስተማር የአለቃ አየለ ፈንታ መሆኑን ነግረው እነሱ ማዳመጥ አለቃ አየለ ደግሞ ጉባኤውን ማካሔድ ጀመሩ:: የፍትሐ ነገሥትን ትምህርት ከጨረሱ በኋላ የሊቃውንት ትርጓሜን በሰፊው ማስተማር ጀመሩ::





የፍትሐ ነገሥትን ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ ከሣሕሌ ወልደ ተክሌ መርሐ ዕውርንና አቡሻክርን ማለትም ምሕዋረ ከዋክብትን ሚጠተ ብርሃናትን የሚያስረዳውን የሊቃውንትን መጽሐፍ ተማሩ:: ይህ ሁሉ ትምህርታቸው የሊቃውንት ቅርስ የሆኑትንና የመምህራኑን ትምህርት የምናመሳክርባቸውን የአራቱን ጉባኤ መጻሕፍት በሙሉ ንባብ ከትርጓሜ የአቡሻሕር መጽሐፍ ከነባለ ሠንሠረዡ ለመጻፍ አስችሏቸዋል:: ይህ ባለ ሠንጠረዥ አቡሻሕር ለኤግዚቢሽን ሌጐስ ተልኮ ለሀገራችን አድናቆትን ስለ ከፍተኛነቱም ሰባት መቶ ሃምሳ ብር ሽልማት አግኝቷል::

## በአዲስ አበባ

ከመንግሥት በ፲፱፻፳፩ ዓ.ም ጥሪ ደረሳቸውና አዲስ አበባ መጡ:: ወደ አዲስ አበባ የመጡት ከአለቃ ኀሩይ ፈንታ ጋር ነበር:: አዲስ አበባም ሁለቱ ሊቃውንት መጻሕፍትን ማስተማርና የሚታተሙትንም መጻሕፍት ከሊቃውንት ጋር ሆኖ ማጠናቀቅ ጀመሩ:: እግረ መንገዳቸውንም አብረዋቸው ከሚሠሩት ሊቃውንት ዕውቀት ይቀስሙ ነበር:: የላሊበላ ገዳማት መምህር ከነበሩት ከመምህር ኀሩይ መጻሕፍተ መነኰሳትን፣ ከመምህር ፊላታዎስ መጻሕፍተ ብሉያትን በሙሉ አጠኑ፤ ከመምህር ገሪማ በኋላ ከአቡነ ሚካኤል የ፲፬ቱን ቅዳሴ አጠናቀው ተማሩ:: ለብዙ ጊዜም አዲስ አበባ አራቱን ጉባኤያት አስተማሩ::

አዲስ አበባ ያሉ ደቀ መዛሙርታቸው የሚኖሩት በየአድባራቱ ነው:: ዶክተር አለቃ አየለ ግን የሚኖሩት ቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ነበር:: ስለዚህ ለማስተማር አለቃ ኀሩይ ወደነበሩበት ወደ መንበረ ልዑል ቅዱስ ማርቆስና ወደ መታሰቢያ ቤት በኣታ ለማርያም ገዳም መመላለስ ነበረባቸው::

ዶክተር አለቃ አየለ በአዲስ አበባ ጉባኤ በሚሔዱበት ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ብቻ ሳይሆኑ ታላላቅ መምህራንም ሁሉ የራሳቸውን ጉባኤ አቋርጠው የእርሳቸውን ጉባኤ ተካፋይ ይሆኑ ነበር::

አዲስ አበባ እያሉ ጣሊያን ኢትዮጵያን ወረረች:: ዶክተር አለቃ አየለ ሁልጊዜ በአሥራ አንድ ሰዓት በቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ቤተ

ክርስቲያን ጸሎተ ሠርክ ሲያደርሱ አንድ ፋሽስት ያያል። እዚህ እየ ቆምክ የምትጸልየው የኢትዮጵያ መንግሥት እንዲመለስልህ በማሰብ ነው» ብሎ እያዳፋ ሲወስዳቸው የሚያውቋቸው ሰዎች አድነዋቸዋል።

በየካቲት ፲፪ ቀን ፲፱፻፳፱ ዓ.ም የፋሽስት መንግሥት የአዲስ አበባን ሕዝብ በጨፈጨፈ ጊዜ ከነደቀመዛሙርታቸው ለዘጠኝ ቀን አሥረዋቸዋል። በዚህ ጊዜ አለቃ እሥረኞችን በማፅናናት ከፍ ያለ አገልግሎት ሰጥተዋል።

ከዚህ ሁሉ በኋላ ወደ ጐንደር ለመመለስ ይወስናል። አለቃ ኀሩይ በዚህ ጊዜ እየደከሙ ነበርና እኔን ሳትቀብረኝ አትሒድ ብለው ይለምናቸዋል። «በሀገሬ ሰው ተክቼ ማለፍ አስቤአለሁና የርስዎም መልካም ፈቃድም ይሁንልኝ አላቸው።» አለቃ ኀሩይም ፈቀዱላቸው። ከመሔዳቸው በፊትም የጐንደር በአታን የእልቅና መዓርግ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ መልካም ፈቃድ ተሰጣቸው። ጐንደርም ሰፊ ጉባኤ አቋቁመው አራቱን ጉባኤያት ማስተማር ጀመሩ። ብዙ ሊቃውንትም አፍርተዋል። የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲም ሰኔ ፲፱፻፷ ዓ.ም የዶክትሬት መዓርግ ሰጣቸው። የሊቃውንት ኮከብም ተባሉ።

## የመጨረሻ ዘመን

ከ፲፱፻፷፩ ዓ.ም ጀምሮ እስከ ዕረፍታቸው ድረስ በዝማሬ፣ የእግዚአብሔርን ስም በማመስገንና ምሥጢራተ እግዚአብሔር በመናገር ቆዩ። እድሜያቸው እየገፋ በመምጣቱ በዚህ ጊዜ የጉባኤው ሥራ እንዲቆምላቸው ተደርገ። ዶክተር አለቃ አየለ በዘመናቸው በርካታ ሊቃውንትን ተክተዋል። በርካታ ጳጳሳትን ሊቃነ ጳጳሳትን እንዲሁም መምህራንን አፍርተዋል።

በአረጋዊነታቸው ላይ ጥቂት ሕመም ተጨምሮባቸው በሕክምና ሲረዱ ቆይተው በአንድ መቶ ሁለት ዓመታቸው ጥር ፲፮ ቀን ፲፱፻፷ ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ። የቀብራቸው ሥነ ሥርዓትም የመንግሥት ባለሥልጣናት፣ የጐንደር ሊቃውንትና የጎንደር ከተማ ሕዝብ በተገኙበት በመንበረ መንግሥት መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን ተፈጸመ።





አስክሬናቸው ካረፈበት ቦታ ላይ ባለአንድ ድርብ የመቃብር ቤት ተሠርቷል። መቃብር ቤቱ የተሠራው ከመድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን ዕቃ ቤት ጋር ተያይዞ ነው የተሠራው። ምድር ቤቱ ውስጥ የማኅበር ጸሎት ጠዋትና ማታ ይደረስበታል፤ ጉባኤም ይካሔድበታል። አንዳንዴም ለምእመናን ትምህርት ይሰጥበታል። ፎቁ ሁለት ክፍሎች አሉት። አንደኛው ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ውሏል። ሁለተኛው ግን የዶክተር አለቃ አየለ የአራቱ ጉባኤ መጻሕፍት በሙሉ ንባብ ከትርጓሜ የሆኑ እንዲሁም ታላቁና ሙሉው ባለሠንጠረዥ አቡሻሕር የሚባለው መጽሐፍ እንግዶች ሲመጡ እንዲያዩት፣ ለአንዳንድ አስፈላጊ ጉዳይ ቅርሶቹ ሲፈለጉም ከዛው በቅርብ እንዲገኙና ተጠብቀው ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፉ ለማድረግ ተቀምጠውበታል።

*ምንጭ፦ መጽሔተ ሊቃውንት ጥር ፲፩ ቀን ፲፱፻፸፪ ዓ.ም*